DEPARTMENT OF HEALTH

# ስለ ሄፓታይተስ ቢ በሚመለከት በተደጋጋሚ የተጠየቁ ጥያቄዎች

## ቁልፍ እውነታዎች

1. የሄፐታይተስ ቢ በሽታ ያለባቸው ብዙ ሰዎች ምንም አይነት የሕመም ምልክት አይታይባቸውም።
2. የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (Centers for Disease Control and Prevention, CDC) ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ምርመራ እንዲያደርጉ ይመክራል።
3. ሄፓታይተስ ቢ የሚተላለፈው ከተበከለ ደም እና ከሰውነት ከሚወጡ ፈሳሾች ጋር በሚኖር ንክኪ ነው።
4. የሄፐታይተስ ቢ ኢንፌክሽንን ለመከላከል በጣም ጥሩው መንገድ ክትባት ነው።

## የሄፐታይተስ ቢ ቫይረስ ምንድን ነው?

ሄፓታይተስ ቢ የጉበት ኢንፌክሽን የሚያስከትል ቫይረስ ነው። ኢንፌክሽኑ ድንገተኛ (አዲስ ኢንፌክሽን) ወይም ሥር የሰደደ (ረጅም ጊዜ የሚቆይ ኢንፌክሽን) ሊሆን ይችላል። ለአንዳንድ ሰዎች ድንገተኛ የሄፐታይተስ ቢ ቫይረስ (Hepatitis B Virus, HBV) ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ሲሆን፣ ድንገተኛ ኢንፌክሽኖች ግን ሥር የሰደዱ ሊሆኑ ይችላሉ።

HBV ከጊዜ በኋላ ከባድ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል፤ ከእነዚህም ውስጥ የጉበት ጉዳት፣ የጉበት ከጥቅም ውጪ መሆን እና የጉበት ካንሰር ይገኙበታል።

አዲስ በHBV የተጠቁ አብዛኛዎቹ አዋቂዎች ኢንፌክሽናቸውን ማዳን ይችላሉ። ነገር ግን በHBV የተያዙ ጨቅላ ሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ኢንፌክሽናቸውን የመፈወስ ዕድላቸው አነስተኛ ሲሆን ብዙውን ጊዜ ሥር የሰደደና የዕድሜ ልክ ኢንፌክሽን ያጋጥማቸዋል።

## የHBV ምልክቶች ምንድናቸው?

ብዙ ሰዎች የሕመም ምልክቶችን አያሳዩም፣ ነገር ግን በሽታውን ለሌሎች ሊያሰራጩ ይችላሉ። ምልክቶቹ የሚታይባቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ምልክቶቹ በበሽታው ከተያዙ በኋላ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት ውስጥ ነው የሚያሳዩት።

ምልክቶቹ የሆድ ህመም፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ ትኩሳት፣ ድካም፣ የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ የቆዳ ወይም የአይኖች ቢጫ መሆን (ጃንዲ)፣ ጥቁር ሽንት እና የሸክላ ቀለም ያለው ሰገራ ሊያካትቱ ይችላሉ።

## HBV ከሰው ወደ ሰው እንዴት ይተላለፋል?

HBV የሚተላለፈው ከተበከለ ደም ወይም ከሰውነት ከሚወጡ ፈሳሾች ጋር በሚኖረው ንክኪ ነው። ይህ ማለት አንድ ሰው በ HBV የተያዘ ሰው ደም ወይም የሰውነት ፈሳሾች ወደ ሰውነቱ ሲገቡ በበሽታው ይያዛል ማለት ነው።

- በእርግዝና ወይም በወሊድ ወቅት ከእናት ወደ ልጅ።
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም ከብዙ አጋሮች ጋር የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በበሽታው የመያዝ አደጋውን ይጨምረዋል።
- እንደ መርፌ፣ ጥጥ እና ማብሰያ ያሉ መርፌዎችን ወይም ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ መጠቀሚያ መሳሪያዎችን ለሌላ ሰው ማጋራት።
- HBV የሚተላለፍባቸው ብዙም ያልተለመዱ መንገዶች እንደ ምላጭ ወይም የጥርስ ብሩሽ፣ የመርፌ መወጋት ጉዳቶች እና ፈቃድ ካለው ተቋም ውጭ የሚደረጉ ንቅሳቶች ወይም መበሳት ያሉ የግል እቃዎችን ማጋራትን  የሚጠይቁ  ድርጊቶችን ያካትታሉ።

ሄፓታይተስ ቢ በሚከተሉት መንገዶች **አይተላለፍም**፦

- የምግብ ወይም የመመገቢያ ዕቃዎችን ለሌላ ሰውማጋራት።
- እንደ መተቃቀፍ፣ መሳም ወይም እጅ ለእጅ መያያዝ ያሉ ቀላል ንክኪዎች።

## HBVን እንዴት መከላከል ይቻላል?

HBVን ለመከላከል በጣም ጥሩው መንገድ ክትባት መውሰድ ነው። HBVን ለመከላከል ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ ክትባት አለ፣ እና የሚከተሉት ግለሰቦች ክትባት እንዲወስዱ ይመከራል፡

- ሕፃናት።
- ክትባት ያልወሰዱ ልጆች።
- ዕድሜያቸው ከ  19-59 የሆነ አዋቂዎች።
- ዕድሜያቸው 60 እና ከዚያ በላይ የሆኑ አዋቂዎች ለሄፐታይተስ ቢ የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው።

የጤና መድህን ለሌላቸው ወይም የክትባት ወጪን የማይሸፍንላቸው ልጆችና አዋቂዎች ነፃ ወይም ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው ክትባቶች ይገኛሉ። ስለ ሚኔሶታ የህፃናት ክትባቶች (Minnesota Vaccines for Children, MnVFC) ፕሮግራም እና ስለ መድህን የሌላቸው እና በቂ መድህን የሌላቸው የአዋቂዎች ክትባት (Uninsured and Underinsured Adult Vaccine, UUAV) ፕሮግራም እና [Where to Get Vaccinated (የት ክትባት መውሰድ እንደሚቻል በተመለከተ) (www.health.state.mn.us/people/immunize/basics/vaxfinder.html)](www.health.state.mn.us/people/immunize/basics/vaxfinder.html) ላይ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።

## የ HBV ምርመራ ማድረግ ያለበት ማነው?

ነፍሰ ጡር ሴቶች በእያንዳንዱ እርግዝና ወቅት የHBV ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ይህ ምርመራ በእርግዝና የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ውስጥ የተጠናቀቀ የሄፐታይተስ ቢ ወለል አንቲጂን ምርመራ (Hepatitis B surface Antigen, HBsAg) ያካትታል።

CDC እድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሄፐታይተስ ቢ ቫይረስን የአንድ ጊዜ ምርመራ እንዲያደርጉ ይመክራል። ምርመራው በሶስት ፓነል መከናወን አለበት። የሶስት ፓነል ምርመራው HBsAg፣ ለሄፐታይተስ ቢ የወለል አንቲጂን (anti-HBs) እና ለ ሄፐታይተስ ቢ ኮር አንቲጂን አንቲቦዲ (total anti-HBc) ያካትታል።

- HBsAg፦ ለ HBV የማጣሪያ ምርመራ። አንድ ሰው በ HBV መያዙን ለማወቅ ይጠቅማል።
- Anti-HBs፦ ለ HBV የመከላከል አቅምን ይፈትሻል። በዚህ ምርመራ ላይ አዎንታዊ ውጤት ከክትባት ወይም ካለፈው ኢንፌክሽን የመከላከል አቅምን ያሳያል።
- Total anti-HBc፦ በዚህ ምርመራ ላይ አዎንታዊ ውጤት ካለ፣ የአሁኑን ወይም ያለፈውን የሄፐታይተስ ቢ ቫይረስ ኢንፌክሽን ያመለክታል።

**ቀጣይነት ያለው ለአደጋ አጋላጭ ምክንያቶች ላሏቸው ሰዎች መደበኛ ምርመራ እንዲያደርጉ ይመከራል።**

## የ HBV ያለበት ሰው ምን ማድረግ አለበት ወይም ማስወገድ አለበት?

HBV ያለባቸው ሰዎች የአልኮል መጠጥን ከመጠጣት መቆጠብ ወይም መገደብ አለባቸው። አንዳንድ መድሃኒቶች ለጉበት መርዛማ ሊሆኑ ስለሚችሉ ማንኛውንም በሐኪም ማዘዣ ወይም ያለ ማዘዣ የሚገዙ መድኃኒቶችን ወይም ተጨማሪ መድሃኒቶችን ከመውሰድዎ በፊት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ማማከር አስፈላጊ ነው።

## ለ HBV የሚሆን ሕክምና አለ?

ለ HBV የሚሆን ምንም አይነት መድኃኒት የለም። ነገር ግን የፀረ-ቫይረስ ህክምና እና በጤና ጥበቃ አቅራቢ የሚደረጉ መደበኛ ክትትሎች HBV ላለባቸው ሰዎች የህይወት ዘመን እና ጥራትን ሊያሻሽል ይችላል።

## HBV ያለበት ሰው ደም፣ ፕላዝማ ወይም የአካል ክፍሎችን መለገስ ይችላል?

አይ፣ አሁን ላይ ወይም ከዚህ በፊት HBV ያለባቸው ወይም የነበረባቸው ሰዎች ደም፣ ፕላዝማ ወይም የአካል ክፍሎችን መለገስ አይችሉም።

Minnesota Department of Health
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414
[www.health.state.mn.us/hepatitis](www.health.state.mn.us/hepatitis)

03/20/2025

*ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት በሚከተለው አድራሻ ይደውሉ፦ 651-201-5414.*